ስለ ተፎካካሪ ፓርቲዎቻችን እና ሐገራዊ ምረጫ

ፓርቲዎች ለሐገራዊ ምርጫ ለመወዳደር መጀመርያ የመወዳደርያ እርካብ /Datum / መሰራት አለበት ምሳሌ - እንደ ዓለም ረዥም ሩጫ ውድድር ሻምፒዮንሽፕ /Championship/ ሁሉም ተወረዳዳሪ ሯጭ በፋይናል ግጥሚያ መወዳደርያ ሜዳ ላይ መግባት /መገኘት አለብኝ ቢባል ትክክል አይሆንም ወይም ልክ ነው አይባልም - እውነትነትም የለውም የሕዝብ ሩጫም አይደለምና - ስለሆነም ማጣርያዎች ይደረጋሉ ቀድሞ በተጠናና በወቅቱ በሚከሰቱ ድምዳሜዎች / መረጃዎች መሰረት ለፋይናል ዙር መድረስ ያለባቸውን ተወዳዳሪ ሯጭበቁጠር እና በብቃት /Minimum Qualification / ይወሰናል / ይነገራል - እርግጥ የስፖርት ውድድርና ሐገራዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምርጫ በቫሉዩ /Value / እና በክብደት የመሬትና የሰማይ ያህል ልዩነት ያላቸው መሆኑ እውነት ቢሆንም የወድድሩ ሂደትና ስነ-ስርዓቱ በትንሹ ቢሆን ተመሳሳይነት አላቸው

ስለሆነም ለፖለቲካ ተፎካካሪዎችም እርካብ መነሻ /Datum / መኖር /መሰራት አለበት -- ለዚህ ምሳሌዎችን ላቅርብ

አንድ - ሁሉም ለሐገራዊ ፖለቲካ ጠርቲ ተፎካካሪነት ብቁ የሆኑ - ኢትዮጵያ በአንድነቷ መቀጠል አለባት, መበታተን / መፈራረስ የለባትም በሚል የወሰነ, የተቀበለ, የሚያምንበት ጉዳይ መሆኑን

ሁለት - ሁሉም ለሐገራዊ ፖለቲካ ጠርቲ ተፎካካሪነት ብቁ የሆኑ - ኢትዮጵያ በሐይማኖታዊ መንግስት /ምሳሌ በሸሪዓ መንግስት/ ሳይሆን በዓለማዊ መንግስት ነው መተዳደር ያለባት በሚባለው ነገር ላይ አቋም የወሰደ መሆኑን

ሶስት - የአንድ ብሄር ወይም ብሄረሰብ ብቻ ስብስብ ፓርቲ ሆኖ በሓገራዊ ምረጫ መወዳደር ትክክል አለመሆኑን ተቀብሎ ከሌሎች ጠርቲዎች ግንባር ፈጥሮም ቁመናው ከምርጫ በፊት መታወቅ አለበት - ምክንያቱም ከነማን ጠርቲዎች ግነባር መፍጠሩ መታወቅ, ለመራጩ ሕዝብ በመፃኢ በወደፊት ጉዳዮች ግለፅንትን ያመጣለታልና /ጠርቲውን በተመለከተ/
ወይም ክምርጫ በኋላ ከቀናኝ ከሌላ አሸናፊ ፓርቲ ጋር ግነባር መፍጠር እችላለሁ ካለም ---- ???
ያም ሆነ ይህ ጠርቲው ኢትዮጵያን ሙሉ ተረክቦ በታምኝነት የማስተዳደር ቁመና አቋም እና ብቃት ያለው መሆን ግልፅ ማድረግ ይጠበቅበታል

አራት / ወሳኝ እና ከባድ ጉዳይ / - የኢትዮጵያ አስተድደር ክልሎች /States / ወሰን, ጊዜም ተወስዶም ቢሆን በሁሉም ተፎካካሪ ጠረቲዎች ስምምነት ተደረሶ ከምርጫ በፊት የክልሎች መስተዳድር ወሰን መተወቅ, መደነግግ, ሕገዊ እውቅና ማግኘት አለበት /መጥሪያ ስማቸው ሳይቀር/ - የአስተዳደር ክልል ወሰን በየወቅቱ በነገስ / ባሸነፈ, ዕድል በቀናው ጠርቲ የሚፈርስ, የሚሻር, የሚቀየር, የሚለወጥ ወዘተ እየሆነ ዘላለም የኢትዮጵያን ሕዝብ ማወክ, ማመስ, ማተራመስ, ማፈናቀል, ማስበርገግ, ማሳመፅ ወዘተ አየገባምና -- እዚህ ላይ ነው, በዚህ ጉዳይ ነው የተፎካካሪ ጠረቲዎች እውነትነት እና ኢትየጵየዊነት ፈተና, / ኅጠኝነት, ጠባብነት, ትምክህተኝነት, ዘረኝነት, አድሎዊነት, ወገንተኝነት, ሹሩድነት, ጠማማነት, ተንኮል, ድብቅነት, ፀለምተኝትነት, አክራሪነት, ዕፈኝነት, ግትርነት, ሤሬኛነት, ጦረኝነት, ስስታምነት, ስግብግብነት /Selfishiness / ወዘተ በሽታዎች ብቅ ብቅ እያሉ ጠርቲዎችን የሚፈታተኑዋቸው

እርግጥ ወደፊት ከግዚያት በኋላ, ምሳሌ - ሁለት ክልሎች መሰተዳድር መቀላቀል መዋሃድ ይሻለናል ይበጀናል ቢሉ ደንብና ሕጎች ክፍት መሆን አለባቸው

አምስት - ኢትዮጵያ በአማርኛ እና በኢንግሊኛ መንግስታዊ ቋንቋ ብቻ መተዳደር አለባት የሚባለው ቀርቶ የብሄር ብሄረሰብ ቋንቋዎች ቢየንስ በተጨማሪ አንድ ቋንቋ በየክልሉ መስተዳድር ይኑር በሚል አቋም የያዘ - አከላሉም የአካባቢ ቋንቋ ከግምት ውስጥ የስገባ መሆን እንዳለበት የተቀበለ የሚያምንበት ጉዳይ መሆኑ

ወዘተ — ወደፊት ተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች የሚወዳደሩት በሐገሪቱ መሰረታዊ እንኳር ጉዳዮች ሳይሆን / ጥልቅ ጥናት ውይይት ተደርጎበት በጠንካራ አስተማመኝ ዋስትና ባለው መሰረት ላይ የታነፀ ያለቀለት ጉዳይ ስለሚሆን / - ወቅቱን በጠበቀ ዓለም በደረሰችበት ርዕዮተ-ዓለም /Ideology / ይሆናል የሚወዳደሩት የሚፎካከሩት

መነሻ ዝቅተኛ እርካብ /Datum / ከሌለ 82 ጠረቲዎች ለምርጫ መቀረብ አለብን ማለታቸው አይቀርም - ወጥነት የሌለው, ከየት እንደሚጀመር የት እንደሚያበቃ የማይታወቅ ወይይት, ምኞት ተስፋ ብቻ /በሰማይ ላም አለኝ ዓይነት/ ጭብጥነት የሌለው, አደናጋሪ, በሕዝብ ደርጃ የማይታወቅ ወይም የተተወ ጊዜ የለፈበት, ለአደጋ የሚጋልጥ ውዥንብሮች የበዛበት ሁኖ - መግባባት, መደራደር, መስማማት አሰቸጋሪ ይሆናል
ከመነሻ እርካብ /Datum / የቀሩ ጥቃቅን ፓረቲዎች ይጠፋሉ ማለት አይደለም - አንድም ከትላልቅ ጠርተዎች ጋር ግነባር ይፈጠራሉ ወይም ትልቅ ፓርቲ እስከንሆን ሕዝባችንን እያስተማርን እየቀሰቀስን እንቆያለን ማለት ይችላሉ

መነሻ እርካብ /Datum / ለመስራት ለመፈጠር ከፍተኛ ልፋት, ድካም, ውይይት, አቅል/ትዕግስት, መግባባት, አርቆ-አሳቢነት ወዘተ ይጠይቃል - መነሻ ዝቅተኛ እርካብ /Datum / የሌለው ውይይት አንዴ ወደ ላይ ከፍ-ከፍ, አንዴ ታጥቦ ጭቃ እየሆነ ወደ ታች እየወረደ - ውይይት ሳይሆን ንትርክ - መግባባት /መደራደር ሳይሆን ሙግት, መስማማት ሳይሆን መነቋቆር እየሆነ አሰልቺ, ጊዜ ገዳይ/አባካኝ, ውጤት-አልባ, ተስፋ-አስቆራጭ ወዘተ. ይሆናል

እንዲህ ደክማቹህ, ለፍታቹህ, በእልህ አሰጨራሽ መሰናክል አልፋቹህ - በአፋችን የምንለው ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር - እውን ማድረግ ከቻላቹህ, ምን ያህል ህሊናቹህ እንደሚደሰት እንደሚረካ, በዚህ ወይም በዚያ ቢባል መለኪያ አታገኙለትም - አጋጣሚ ሁኖ በዚህ ወቅት እናንት ሁናቹህ ተገኝታቹህ ታሪክ ከሰራቹህ - ታሪኩ ዝም-ብሎ ተራ ታሪክ ሳይሆን እየተባለ እየተነገር እንደቆየው አሁንምያለው ምኞት - ይህ ጊዜ -ቀን እንደ መስከረም ሁለት /የደረግ/ ወይም እንደ ግንቦት ሃያ /የኢህደግ/ ዓይነት የሚሻር, የሚቀር, የሚተው ሳይሆን የኢትዮጵያ ትንሳኤ ቀን ሁኗልና ዘላለም በየዓመቱ ቀኑ ይከበራል እናተም ትዘከራላቹህ -- ይቅናቹህ!

/NEXT / ከጋራ አቋም እና ስምምነት በኋላ
ተፎካካሪ ፓረቲዎች በምን በምን ሊለያዩ, ሊቦደኑ, ሊሸነሽኑ, ጎራ ሊፈጥሩ ይችላሉ

1 - በመሬት እና ይዞታ ጉዳይ ላይ
2 - የኢትዮጵያ የወደብ ባለቤትነት ጉዳይ ላይ
3 - በቡድን እና በግለሰብ መብት ላይ
4 - በሴቶች መብት ጉዳይ ላይ
5 - በሐገር መከላከያ እና ደሕንነት ጉዳይ ላይ
6 - በበጀት እና በኦዲቲንግ ጉዳይ ላይ
7 - በግብር, ታክስ, እና ጉምሩክ ጉዳይ ላይ
8 - በፋይናንስ በባንኮች ጉዳይ ላይ
9 - በሚንስትር መ/ቤቶች ጉዳይ
10 - በሐገራዊ ልማት እና ፕሮጀከቶች ጉዳይ
11 - በከተሞች እና በገጠር አስተዳደር ጉዳይ
12 - በመሠርተ-ልማት ላይ
13 - በውጭ ሀገራት ግኑኙነት ፖሊሲ ጉዳይ ላይ
14 - ሶሻል ሰኩሪቲ ፈንድ ጉዳይ ላይ --- ወዘተ.

≡ የኢትዮጵያ መንግስት ዓይነት /አሓዳዊ, ፌደራለዊ,, ፕረዘደንሻል, የቡዙሓን ፓረቲ, ወዘተ/ ምን ዓይነት ይሁን ጉዳይ በየምረጫ ጊዚያት ለመረጫ የሚቀርብ መሆን ስሌለበት ከላይ እንደገለፅኩት የኢትዮጵያ አስተድደር ክልሎች ወሰን /States / ጊዜም ተወስዶም ቢሆን በሁሉም ተፎካካሪ ጠርቲዎች ስምምነት ተደረሶ ከምርጫ በፊት የክልሎች መስተዳድር ወሰን መተወቅ መደነግግ ሕገዊ

እውቅና ማግኘት ስላለበት /የመ.ክልል ሲያሚያቸው ጭምር/ - በዚህ ስምምነት/ውሳኔ ጊዜ የመንግስታችን ዓይነት ይታወቃል /ይወሰናል /ግልፅ ይሆናል

የተፎካካሪ ጠርቲ አባላት የሆናቹህ ለውይይት ጥዋት ከቤታቹህ ስትወጡ ፀልዩ, ኢትጵያ ለዘላለም ትኑር ትንሳዔዋን አሳየን በሉ -- ከእናንተ በተቃራኒው ያሉ ደግሞ እትብታቸው የተቀበረው ኢትዮጵያ ምድር መሬት አፈር ውስጥ ሆኖ እያለ ልባቸው ባህር ተሻግሮ ውጭ ሀገራት የኮበለለባቹህ ልብ ይስጣቹህ - የቀለዋጭነት ስሜት ህሊናችሁን ዘወትር ከሚርበሻቹህ የራሳቹህ ለራሳቹህ መሬት ብታስቡ ብትጨነቁ በትታክቱ ብተደክሙ በትፀልዩ ወዘተ. በምድርም በሰማይም ዋጋ የሚያሰጣቹህ ይሆናል, አሁንም ደግሜ ልብ ይስጣቹህ እላለሁ

ስለ የሚጋጩን ነገሮች
ውይይታችን ስለ ካልኩለስ /Calculus / ወይም ስለ ወባ በሽታ አይደለም, ስለ ማህበረ-ሰብ ሕዝብ አስተዳደር መንግስት ነው - መንግስት እንደ ዝናብ ከሰማይ የሚወርድ ሳይሆን እኛ ሰዎች የምንቀርፀው, የምናበጃጀው, የምንሰራው, የምንፈጠረው ወዘተ. ነው - የአስተዳደር አከላለል ለማህበረ-ሰብ ሕዝብ ፍላጎት እና ደስታ መሆን አለበት //የማንነት ጥያቄ-ጉዳይ ተወደደም ተጠላም ከስብዕና እና ከሞራል ጋር የተያያዘ ነው// ሞራል የሌለው የጎደለው ማህበር-ሰብ ሕዝብ ከንቱ ነው - ስብዕናውን መብቱን ማስከበር አይችልም -- ይህን ጠላት ወራሪ ሀይል እንደ መሳሪያ ይጠቀምበታል - ምሳሌ የቀኝ-ገዥዎችን ቅሬት /ጠባሳ በአንዳድ ሃገራት የሆነውን ያለውን ነገሮች ማንሳት ይቻላል /Human Identity Crisis / -- እኛማ ምስጋና ለቀደምት አርበኞቻችን አትዮጵያውያን ኩሩ ነን ሞራላችን ብዙም የተጎዳ አይደለም, ለስብዕናችን ከፈተኛውን ዋጋ እንስጣለን - እናማ ይህ ጉዳይ ስንፈልግ የምናስተናግደው ሳንፈልግ የምናስቀረው ጉዳይ ሳይሆን - የሰው ልጅ ስብዕና / Human Dignity / ከማንነት ጥያቄ ይወለዳል ይመነጫል ይፈጠራል እና አንቀልድ
በተለይ በዚህ ሽግግር ወቅት ተፎካካሪ ጠርቲዎች ውይይታቸው ግልፅ እና እውነት ፍርጥርጥ ያለበት ዓይነት መሆን ነው ያለበት, ይህ አጋጣሚ መቸም አይገኝም - ድብብቆሽ ጨዋታ ይቅር ለቀጣይ ትውልድ የተሸፋፈነ, የተከዳደነ, የተደፋፈነ, የተሸሸገ, የተቀባባ, ወዘተ. ነገር ማቆየት, ማስተላለፍ, ማውረስ አይገባም // ይቅር መባበልን ባሕላችን እና መሳርያችን አድርገን እውነትን እንፈልጋት እናግኛት እንወቅ //

እንደ ግለስብ ከሆነ ከተወለደበት ቀየ ይልቅ በሌላው የኢትዮጵያ ክልል ተቀንቀሳቀሶ ሂዶ መስራት ነው የሚፈልገው - ሕገ-መንግስታችን ዜጋ በየትኛውም ኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ሰርቶ ሃብት አፍርቶ የመኖር ነፃነት ሙሉ መብት የተረጋገጠ አስተማማኝ ዋስትና ያለው መሬት ያለ እውነት ሃቅ መሆን አለበት // ለኢትዮጵያ ጠንካራ አንድነት መተሳሰር አንዱ ትልቁ ምሰሶ ይህ ሕግ ፍትሕ ነፃነት ነው // በዚህ ላይ በጥልቅ በሰፊው መሰራት አለበት
በቀየህ ሰርተህ ሃብት ለማፍራት ብዙ የማመቹ ነገሮች እኮ አሉ የራስህ ሰዎች ጭምር የፈታተኑሃል እውነት ነው እየሱስ-ክርስቶስ በቀየው ሲያስተምር የገጠመው ይኸው ነው, በራሱ ሰዎች ይሄ ደግሞ ማን ነው አናውቀውም እንዴ የዛ የአናጢው ልጅ አይደለምን - የማርየም ልጇ ነው እንኳ አላሉትም

በጊዜው የተከሰቱ ያሉትን የማህበረ-ሰብ ሕዝብ አስተሳሰብ በወቅቱ ማስተናገድ ማስታመም እንጂ መናቅ ተገቢ አይደለም - አሁን በታላቋ እንግሊዝ እየተከሰተ ያለው የአየረላነድ እና እስኮትላነደ ችግር ዓይነት መምጣት የለበትም - ሃያል ወይም የበለፀገ ሐገር መሆን ብቻውን ከማህበረ-ሰብ ሕዝብ አስተዳደር ጥያቄ አያድንም /በራሻም እንዲሁ/ - እኛም ከባድ የማህበረ-ሰብ ሕዝብ አስተዳደር ጥያቄ ለቀጣይ ትውልድ ማስተላለፍ የለብንም - አሁኑኑ ማለፍያ መፍትሂዎች መድረግ, መስራት, መበጀት ወዘተ. አለባቸው - ለአንድነታችን ጠንካራ መስረት ይሆናሉና - ፍቅር በፍቅር እንሆናለን, ጎረቤቶቻችን እሰኪቀኑብን ድረስ
'አይመጣምን ትተሽ ይመጣልንም አስቢ' እንደሚባለው

ይቀጥላል -:

ትንሳዔ ደረሰ
ጥር 2011 ዓ.ም